# ምርጫውን ሠላማዊና ተዓማኒ ለማድረግ

**በሽር አህመድ**

12-23-14

በቅርቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን አካሂዶ ነበር። ምክር ቤቱ ከተቋቋመ ጀምሮ እስካሁን ባለው ሂደት እየተገናኘ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ይመክራል። ይህ በአገራችን ታሪክ በአዲስ ምዕራፍ ውስጥ የተወጠነ ሌላ ታሪካዊ ምዕራፍ መሆኑ ለማንም እሙን ነው።

የአገራችን ፖለቲካ ከጥላቻ ፖለቲካነት ወደ ህይወት ያዘለ የፖለቲካ ፍትጊያ ለመቀየር መሠረት የሚጥል ነው። እንደሚታወቀው ሁሉ ቀደም ሲል በአገራችን በሰፊው የነበረውና አሁንም በተወሰኑ ወገኖች እየተንፀባረቀ ያለው የፖለቲካ ትግል ጭፍን ጥላቻ ነው። የሚቀርበው ተቃውሞም ለተቃውሞ ተብሎ የሚደራጅ መሆኑን ህዝቡ እየተማረው እያወቀው መጥቷል። የተሰራ አልተሰራም፣ በዓይን የሚታይ የሚጨበጥና ያለ ነገር የለም በሚል ጭፍን ክርክር ይካሄድ እንደነበር ይታወቃል።

የአገሪቱን ሕገ መንግሥት ተከትሎ ከመስራትና ለሕዝብ የፖለቲካ አማራጭን አቅርቦ በሃሳብ ልቆና ይበጀናል የሚል ስሜት በህዝብ ዘንድ አሳድሮ ለመመረጥ ከመሞከር ይልቅ ብጥስጣሽ መሠረት የሌለውን የጥላቻ ሃረጎችን እየገጣጠሙ ሸውዶ ለማለፍ ወይም ሕገ መንግሥቱ በማይፈቅደው መንገድ ወደ ህዝብ ኃላፊነት ለመምጣት የሚደረገው ጥረት ቀደም ሲል ጎልቶ ይታይ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በሁለት ጎራ በመከፈላቸው በአገሪቱ ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ እየቀየረው ይገኛል።

በአንድ በኩል በሕገ መንግሥቱ ጥላ ሥር ሆነው በአገራቸው ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳይ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ የሚፈልጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች

ተፈጥረዋል። እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከገዢው የፖለቲካ ድርጅት ጋር በአገራቸው ጉዳይ መሆን በሚገባው ነገር የሚወያዩበት መድረክ መፍጠር ችለዋል።

የምርጫ ሂደቶች ምን መመምሰል እንዳለባቸውና አባላቶቻቸው ምን ዓይነት ሥነ ምግባር ሊያሟሉ እንደሚገባቸው የጋራ መግባቢያ ሰነድ ፈርመዋል። ይህንን ሰነድ ለአባላቶቻቸው በማስተማርም በአገሪቱ ነጻ፣ ዴሞራሲያዊና ፍትሃዊ ምርጫ ማካሄድ እንዲቻል የተቻላቸውን ያህል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ችግሮች ቢያጋጥሟቸው እንኳን በውይይት ለመፍታት የሚያስችላቸውን አሠራር በጋራ መዘርጋት ችለዋል።

በዚህ መልክ የአገራችን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት እየተጠናከረ እንዲሄድና ሕዝብ ከሚቀርቡለት በርካታ አማራጮች ይጠቅመኛል ያለውን ለይቶ መምረጥ እንዲችል አመቺ ሁኔታ መፍጠር የተቻለበት ሁኔታ ፈጥረዋል። በዚህ ረገድ በአገራችን ታማኝ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ስብስብ እየተፈጠረ መሆኑን ያሳየናል።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን የስምምነት ኮድም ሆነ ተባብሮና ተጋግዞ መሥራት የማይፈልግ ጭፍን የፖለቲካ ጥላቻ የሚያራምድ ኀራ በተወሰኑ የዲያስፖራ አባላት ተንጠልጥሎ አገሪቱ ምንጊዜም ሠላም እንዳታገኝ ከሚሹ ወገኖች ኀራ ተሰልፎ ጽንፈኛ እንቅስቃሴ የሚያደርግ የፖለቲካ ድርጅት መኖሩ እሙን ነው።

ይህ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት በአገሪቱ ሕገ መንግሥት ጥላ ከለላ መመሥረት ቢችልም አጠቃላይ ድርጊቱ ግን ሕገ መንግሥቱን የመናድ ተግባር ነው። በአገሪቱ ጭፍን የፖለቲካ ዘመቻ ማካሄድ ነው። በአገሪቱ የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎችን መቃወም ነው። ከሽብርተኞችና ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር በመተባበር በአገሪቱ ሠላም እንዳይኖር የሁከትና የብጥብጥ አጀንዳ መፍጠር ነው።

በዚህ መልክ ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዳይካሄድ የማሰናከል ሥራን ያከናውናል። ህዝብን የማወናበድና ትክክለኛ ያልሆነ መንገድ እንዲከተል የማድረግ ስልቶችን ነድፎ ይንቀሳቀሳል። በዚህ ጽሁፍ ትኩረት ለመስጠት የተፈለገው ግን ለሁለተኛው ቡድን አይደለም።

በአገሪቱ በሠላማዊ መንገድ የጋራ መድረክ ፈጥረው እየተንቀሳቀሱ ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች የሰሞኑ ውይይትና ከመራጩ ኅብረተሰብ ምን እንደሚጠበቅ ለመጠቆም ያህል ነው። በአገሪቱ የተረጋገጠው የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል ገዢው ፓርቲ ያልተቆጠበ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። የዘንድሮው ምርጫ እንዳለፉት ምርጫዎች ደረጃውን የጠበቀ፣ ነጻ፣ ፍትሃዊና በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ የተቻላቸውን ያህል እንደሚንቀሳቀሱና በዚህም  ሕገ መንግሥቱንና በጋራ ያወጡትን የምርጫ ሥነ ምግባር መርህ እንደሚከተሉ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

እንደሚታወቀው ለአንዲት አገር የሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት መረጋገጥ ወሣኙ ነገር የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መጠናከር ነው።  የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት በተዘረጋበት አገር ማንኛውም አካል ወደ ሕዝብ ኃላፊነት የሚመጣው ሕዝብና በሕዝብ ምርጫ ብቻ ይሆናል። ይህ ተረጋገጠ ማለት ደግሞ ሕዝብ ይጠቅመኛል ያለውን የሚመርጥበት አይበጀኝም ያለውን የሚያወርድበት ሥርዓት ሰረፀ ማለት ነው። እነዚህ ነገሮች ሲረጋገጡ የሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት ተረጋገጠ ማለት ይቻላል።

የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት በአገራችን ላለፉት ዓመታት ተግባራዊ መሆን ችሏል። ሕዝቡም የሥልጣን ባለቤትነቱን በሚገባ ሲተገብረው ቆይቷል። በአገራችን የፖለቲካ ታሪክ ከሁለት አሥርት ዓመታት በፊት የተጀመረው የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት አሁን ላይ ቆመን ስንመዝነው የማይናወጥ መሠረት መጣሉን መረዳት ይቻላል።  የሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት  ተረጋገጠ የሚባለው  በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኖረው የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለሕዝብ እያስተዋወቁ ሕዝብ

ይጠቅመኛል፣ ይበጀኛል ያለውን መምረጥ ሲችል ነው። ሕዝቡ አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አግኝቶ አንዱን ከአንዱ በማነጻጸር መምረጥም ሆነ መጣል የሚችልበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው።

የተለያየ አጀንዳ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የአገሪቱ ሕገ መንግሥት በሚፈቅደው መሠረት በመደራጀት አጀንዳቸውን ለሕዝብ በማቅረብ መመረጥ የሚችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው። በዚህ መልክ ዜጎች እንደየፍላጎታቸው የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን በመመሥረት በአገራቸው የፖለቲካ ሥርዓት በነጻነት ተሳታፊ መሆን ከቻሉ የሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት መረጋገጡ እውን ሆነ ማለት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነቱን ተነጥቆ ኖሯል። ባለፉት ሥርዓታት የነበረው ሁኔታ ሲቃኝ መንግሥታት በጠመንጃ አፈሙዝ የሕዝብን የፖለቲካ ሥልጣን አፍኖ የሥልጣን እድሜውን ሲያራዝም ኖሯል። ፈላጭ ቆራጭ መሪዎችን ማስተናገድ ለኢትዮጵያውያን የተሰጠ ፀጋ ይመስል በርካታ ዓመታት በዚህ ሁኔታ አልፈዋል፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ ለዘመናት ነግሶ የነበረውን የአፈና ሥርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሥር መሠረቱ በ1983 ዓ.ም ከተናደ በኋላ የተፈጠረው የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መሠረቱ እየተጠናከረ መጥቷል። በአፍሪካ አህጉር ተወዳዳሪ ያልነበረውን ግዙፍ ሠራዊት በመገንባት አምባገነንነትንና ጭቆናን በአገሪቱ አስፍኖ የነበረው ሥርዓት ተገርስሶ በኢትዮጵያ የተጻፈው ደማቅ ታሪክ እየተጠናከረ መጥቶ ከማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ደርሷል። የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሠላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ባልነበረባት ኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መገንባት አልጋ በአልጋ እንዳልሆነ ይታወቃል። ቀደም ሲል የነበረው ተሞክሮም የራሱን ጫና ማሳደሩ አይቀሬ ይሆናል።

እንደሚታወቀው ሁሉ አገሪቱ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የበላይነት የነገሰባት አገር ነበረች። በወቅቱ የነበረው ፓርቲ ከሚከተለው የፖለቲካ አመለካከት የተለየ ሃሳብ ማመንጨትም ሆነ ማራመድ በሕግ የተከለከለ ነበር። የተለየ ሀሳብ ማመንጨት ፈጽሞ አይታሰብም ብቻ ሳይሆን በሕግ የሚያስቀጣና የሚያስኮንን ነበር፡፡ የዜጎች

የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት የታፈነበት ዘመን ስለነበር ምርጫ ይባል የነበረው የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት በብዛት ይቀርባሉ፤ ከእነሱ መካከል ምርጫ ይካሄዳል። በአገሪቱ የአኃዳዊ ሥርዓት አስተሳሰብ የነገሰበትና ዜጎች የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነታቸው የተነጠቀበት ሁኔታ ነበር።

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አገር ነች። በአገሪቱ 75 ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሕጋዊ እውቅና አግኝተው በፌዴሬሽን ምክር ቤት መቀመጫ ወንበር እንዳላቸው መረጃዎች ያሳያሉ።

ቀደም ሲል የነበረውና ዜጎች  ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ለመጠቀም የማይችሉበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተቀይሮ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን የማሳደግና የማዳበር ሥራ አጠናክረው እየተገበሩት ይገኛሉ፡፡ ባለፉት አሥርት ዓመታት በተደረገው ጥረት በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት እውን ሆኗል፡፡ የተለያየ የፖለቲካ እምነት ያላቸው በርካታ ፓርቲዎች ተፈጥረዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በአሁኑ ወቅት 75 የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕጋዊ መንገድ ተመዝግበው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡

በአገሪቱ ይህንን ያህል የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖራቸውና ተሳትፎ ማድረጋቸው የሚያሳየው ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ነው። አንደኛው ዜጎች በፈለጉበት የፖለቲካ ድርጅት አባል የመሆን መብታቸው መረጋገጡ ሲሆን ሌላው ደግሞ በአገሪቱ ያለው የፖለቲካ ምህዳር እየሰፋ መምጣቱን ነው።  በመጀመሪያው የተቀመጠው ነጥብ ዜጎች በተፈጠረው ሰፊ የፖለቲካ ምህዳር ተጠቅመው እንደየፍላጎታቸው በሚያምኑበት የፖለቲካ አጀንዳ ሥር በመደራጀት በአገራቸው የፖለቲካ፣ ምጣኔ ሀብትና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ድርሻቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸው ሁኔታ መፈጠሩን ያሳያል።

በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰው ደግሞ በአገሪቱ ወደ ሥልጣን መምጣት የሚቻለው በሕዝብ ፍላጎትና ምርጫ ብቻ መሆኑ የተጋገጠበትን ሁኔታ ማየት የሚቻልበት አቅጣጫ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል። በዚህ መልክ በአገሪቱ የዜጎችን ዴሞክራሲያዊ መብት የሚያረጋግጥ  ሥርዓት መፈጠሩንና ሥርዓቱ እየተጠናከረ መምጣቱን ነው የሚያሳየው፡፡ ባለፉት ዓመታት የታየውና የተረጋገጠውም ይኸው ነው፡፡ በዚህ

መልክ በአገራችን አራት አገራዊ፣ ሦስት የአካባቢና በርካታ የሟሟያ ምርጫዎች ተካሂደዋል፡፡

የመጀመሪያው ታሪካዊ ምርጫ የተካሄደው በ1987 ዓም ነበር። በዚያን አገራዊ ምርጫ 57 የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፈዋል። ምርጫው የመጀመሪያው መድብለ ፓርቲ የተሳተፉበት ምርጫ መሆኑ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ነበር። ምርጫው ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ነጻና በአገሪቱ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የከፈተ ነበር፡፡

ፍጹም ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ የነበረው የ1987ቱ ምርጫ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የዓለም ኅብረተሰብንም ጭምር ያስገረመና በአገሪቱ የሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነትን ያረጋገጠ ነበር፡፡ በአገሪቱ ለሁለተኛ ጊዜ በ1992 ዓ.ም ምርጫ ተካሄደ። በዚህ ምርጫ 49 የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፈዋል፡፡

ምርጫው እንደ ቀዳሚው ሁሉ ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ነበር፡፡ ሕዝቡ በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠለትን የፖለቲካ ሥልጣን በመጠቀም ይጠቅመኛል ያለውን የፖለቲካ ፓርቲ በአገሪቱ ታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ መርጧል፡፡

1997 ዓ.ም ሌላው ታሪካዊ አገራዊ ምርጫ የተካሄደበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህ ዓመት በአገሪቱ ተመስርቶ ሥር እየሰደደ የነበረውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ለመናድ የተነሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተሳተፉበት ምርጫ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሕገ መንግሥቱን ሕገ ወጥ በሆነ መልክ በመናድ ሥልጣን ለመቆናጠጥ ከፍተኛ ጥረት የተደረገበት ወቅት ነበር።

በዚህ አገራዊ ምርጫ አንድ ብሄር፣ ብሄረሰብና ሕዝብ በሌላው እንዲነሳሳ፣ አገሪቱ ውስጥ የነበረው ሠላም እንዲደፈርስ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከሠላምና ልማት ወጥተው መቋጫ በሌለው የእርስ በርስ ጦርነት እንዲዘፈቁ ለማድረግ ያልተሞከረ ነገር አልነበረም። በሦስተኛው አገራዊ ምርጫ 36 የፖለቲካ ድርጅቶች መሳተፋቸው የታሪክ ማህደራት ያሳያሉ።

በ2002 ዓ.ም የተካሄደው አራተኛው አገራዊ ምርጫ ከሦስተኛው አገራዊ ምርጫ የሚለየው በሦስተኛው አገራዊ ምርጫ ከ130 በላይ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አባላት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ ያገኙ ሲሆን በአራተኛው አገራዊ

ምርጫ የተሳተፉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር 63 ቢሆንም ከተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት የተመረጠው አንድ አባል ብቻ ነበር፡፡

በአገሪቱ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ከተዘረጋበት ከ1983 ዓ.ም ወዲህ የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት አክትሟል። ቁጥራቸው ቀላል የማይባል የተለያየ አጀንዳ ያነገቡ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመስርተዋል፡፡ ሆኖም በአኃዳዊ አስተሳሰብ የሰከሩ ስብስቦች በተከፈተላቸው ሜዳ መጋለብና በአገራቸው የፖለቲካ ኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ የቻሉትን ያህል አስተዋጽኦ ማድረግ ሲጠበቅባቸው የመድበለ ፓርቲ ሥርዓቱን ለመፈታተን ያላደረጉት ጥረት ባይኖርም እያደር እየከሰሙ የመጡበት ሁኔታ ተፈጥሮ በአገራችን አስተማማኝ የመድበለ ፓርቲና ፌዴራል ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

ያለፉት ምርጫዎች ከነበሩባቸው ክፍተቶች መሻሻል የሚገባው ሌላው ነጥብ ደግሞ የባለ ድርሻ አካላትን አቅም መገንባት ነው። ከዚህ አንጻር የኅብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል።

ከዚሁ ጎን ለጎን የፖለቲካ ፓርቲዎች የአገሪቱን ሕገ መንግሥት አክብረው ከመንቀሳቀስ አንጻር የተለያያ ሥልጠና የመስጠት አቅጣጫ ተይዟል። የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያየ ሥልጠና የሚያገኙበትና በመካከላቸው ያለውን ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ መግባባት እንዲኖርና በሠላማዊ መንገድ ሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነቱን እንዲጠቀም ለማስቻል የምክክር መድረኮች ይዘጋጃሉ። በዚህ መልክ የተለያዩ መድረኮች ይዘጋጃሉ ተብሎ ይጠበቃል፤ ገንቢ ውይይቶችም እንደሚካሄዱ እንዲሁ፡፡

ምርጫ 2007 እንደቀደሙት ምርጫዎች ነጻ፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሊሰሩም ይገባል። በአገሪቱ እውን መሆን የጀመረውን የሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት ይበልጥ በማጎልበት፣ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የሚያስችል ቀጣይነት ያለው ልማት በማረጋገጥ አገሪቱን ወደ ላቀ የእድገት ምህዋር ለማሸጋገር የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አንድነታቸውን አጠናክረው ሊሰሩ ይገባል።

ባለፉት ምርጫዎች ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነቱን በተገቢው መንገድ ያረጋገጠበት ሁኔታ ታይቷል። በመጀመሪያው ታሪካዊ ምርጫ ለመምረጥ የተመዘገበው ሕዝብ ብዛት 21 ሚሊዮን 340 ሺህ ያህል ነበር፤ የመረጠው ደግሞ ወደ 20 ሚሊዮን ይደርስ ነበር። በዚህ ምርጫ 43 የፖለቲካ ፓርቲዎችም የፓርላማ መቀመጫ ማግኘታቸው ይታወሳል፡፡

በሁለተኛው ምርጫ ደግሞ 22 ሚሊዮን የሚጠጉ መራጮች ተመዝግበው ከ19 ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ በላይ የሚሆኑት መርጠዋል፡፡ 42 የፖለቲካ ድርጅቶችም በፓርላማ ውስጥ መቀመጫ አግኝተዋል፡፡ በ1997 እና በ2002 ደግሞ 27 ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ያህልና 32 ሚሊዮን የሚደርሱ መራጮች ተመዝግበዋል፤ እንደየቅድመ ተከተላቸውም ከ22 ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ በላይና 30 ሚሊዮን የሚደርሱቱ መምረጣቸውን ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተገኘ መረጃ ያሳያል።

ከቀረበው አኃዛዊ መረጃ ማየት እንደሚቻለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነቱን በሚገባ እየተጠቀመ መጥቷል። ከአንድ ምርጫ ወደ ቀጣይ ምርጫ በሚገባበት ወቅትም የመራጭ ቁጥር እያደገ መምጣቱን መገንዘብ ይቻላል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ኅብረተሰቡ አጠቃላይ በአገሪቱ የተፈጠረውን ዴሞክራሲያዊ መብቱን በመጠቀም ይበጀኛል ያለውን ለመምረጥ ተሳትፎውን እያሳደገ መምጣቱን መገንዘብ ይቻላል። በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1987 ዓ.ም ምርጫ ሲካሄድ የነበረው መራጭ ቁጥርና በ2002 ዓ.ም የነበረው በሚናነጻፀርበት ጊዜ መሠረታዊ ለውጥ ያሳያል። የ2002 ዓ.ም ምርጫ ከ1987 ዓ.ም ምርጫ ጋር ሲነጻፀርም ከአሥር ሚሊዮን በላይ መራጭ ልዩነት እንዳለው ነው፡፡

ይህ የአገራችን ሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣኑን በአግባብ እየተጠቀመበት እንዳለ የሚያሳይ ነው። ከነበረው የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ፈላጭ ቆራጭነትና በአፈሙዝ ኃይል የታገዛ አገዛዝ ተላቆ ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተረጋግጦለትና በአገራችን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት እውን ሆኖ ዜጎች አንድም በሚያምኑበት የፖለቲካ ድርጅት የመሳተፍ መብታቸው ተከብሮላቸው በሌላ ወገን ደግሞ የሚመራቸውን

የፖለቲካ ድርጅት ሥልጣን የመስጠትና በትክክል አይሰራልንም ያሉትን የማስወገድ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነታቸውን ያረጋገጡበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

በዚህ መልክም እስካሁን የነበሩት ምርጫዎች በውጤታማነት ተጠናቀዋል። በዘንድሮው ዓመት ለሚካሄደው ምርጫም ሕዝቡ እንደተለመደው ሁሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አጀንዳዎች በሚገባ በመመርመር በነቂስ ወጥቶ ሊመዘገብና ድምጹን ሊሰጥ ይገባል።

የአንድ ዜጋ ድምጽ ትልቅ ዋጋ አለው። በመሆኑም ሁሉም እድሜው 18 እና ከዚያ በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ ምርጫውን ለመምረጥ ከወዲሁ ዝግጅት ሊያደርግ ይገባል። ይህ የሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት እየተጠናከረ መጥቶ በአሁኑ ወቅት ሥር የሰደደበት ሁኔታ ቢኖርም አንዳንድ አፍራሽ ወገኖች ሕዝቡ የመምረጥ መብቱን እንዳይጠቀምበት በሰንካላ ምክንያቶች ሊያወናብዱት ላይ ታች ሲሉ ይስተዋላሉ።

ይህ ግን ለአገራችንም ሆነ ለሕዝባችን የሚጠቅም ባለመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አጀንዳዎች በሚገባ በመመርመር ይጠቅመኛል የሚለውን ፓርቲ ለመምረጥ አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረገ መጠበቅና እለቱ ሲደርስም በከፍተኛ ተሳትፎ ምርጫውን ማከናወን ይኖርበታል።